የኢትዮጵያ
ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL (EHRCO)

**አስቸኳይ ጋዜጣዊ መግለጫ**

# ከሀይማኖት ጋር ተያይዞ ባለው ወቅታዊ የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ከኢሰመጉ የተሰጠ መግለጫ

ጥር 30/2015 ዓ.ም

## መግቢያ፡

ኢሰመጉ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ጋር ተያይዘው የሚነሱ የሰብዓዊ መብቶች ጉዳዮችን ሲከታተል የቆየ ሲሆን ከእዚህም ጋር ተያይዞ እሁድ ጥር 14 ቀን 2015 ዓ.ም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቅዱስ ሲኖዶስ እውቅና ባልተሰጣቸው ሶስት ሊቃነ ጳጳሳት አማካኝነት 26 ኤጲስ ቆጶሳት የተሾሙ ሲሆን ይህንንም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ህገ-ወጥ ያለውን ድርጊት ተከትሎ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በዋናነት በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ አብያተክርስቲያናት ውስጥ ከቅዱስ ሲኖዶሱ እውቅና ያልተሰጣቸው አዲስ የተሾሙ ኤጲስ ቆጶሳት ወደ አብያተክርስቲያናት በመንግስት የጸጥታ አካላት ጭምር ታጅበው በመግባታቸው እና ምዕመኑ ይህንን ባለመቀበሉ ምክንያት በተፈጠሩ ግጭቶች በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ አካባቢዎች የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተፈጽመዋል፡፡ ለማሳያነት በሻሸመኔ ከተማ ከመንግስት የጸጥታ አካላት በተተኮሱ ጥይቶች የሰዎች ህይወት ማለፉን፣ የአካል ጉዳት መድረሱን እንዲሁም በያቤሎ አካባቢ በቤተክርስቲያኒቱ አገልጋዮች ላይ ጭምር እስራት፣ ማዋከብ እና ድብደባ መፈጸሙን እና በተለያዩ አካባቢዎች ይህንን አካሄድ በተቃወሙ የእምነቱ ተከታዮች ላይ እና የቤተክርሲቲያኒቱ አገልጋዮች ላይ ድብደባዎች እንደተፈጸሙ፣ ቤት ሰብሮ በመግባት የህግ ስነስርዓትን ያልተከተሉ እስራቶች እንደተከናወኑ እና በርካታ ቁጥር ያለቸው ሰዎችም በብዛት እየታሰሩ መሆኑን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡

በተጨማሪም ከቅዱስ ሲኖዶሱ በተላለፈ መልእክት መሰረት ጥቁር ልብስ የለበሱ ሰዎችን በአንዳንድ አካባቢዎች እስራት፣ እንግልት እና መዋከብ እየተፈጸመባቸው እንደሆነና ይህንንም ድርጊት አንዳንድ ተቋማት እና ድርጅቶች በተመሳሳይ መልኩ እየፈጸሙት መሆኑን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡ ስለሆነም ይህ ጉዳይ ወደየማይሆን አቅጣጫ በመሄድ ተባብሶ ከፍተኛ የሰውና የንብረት ጥፋቶችን ከማስከተሉ በፊት የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲያደርጉና የበኩላቸውን ሀላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡ ኢሰመጉ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ በደረሱ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ ተጨማሪ የምርመራ ስራዎችን በመስራት ዝርዝር ዘገባ የሚያዘጋጅ መሆኑን ከወዲሁ ይገልጻል

## ተያያዥ የህግ ድንጋጌዎች፡

የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 27 የሀይማኖት ነጻነት መብትን የያዘ ሲሆን በአንቀጽ 11(3) ላይ መንግስት በሀይማኖት ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገባ እና ሀይማኖትም በመንግስት ጉዳይ ላይ ጣልቃ እንደማይገባ ይደነግጋል፡፡ የእዚህ ንዑስ አንቀጽ ዋነኛ አላማ ከህገ መንግስቱ ማብራሪያ መረዳት እንደሚቻለው ሀይማኖትን ከመንግስት ጣልቃ ገብነት እና ከፖለቲካ ጫና ነጻ እንዲሆን በማድረግ የዜጎችን የእምነት ነጻነት ላለመገደብ ሲሆን መንግስት በሀይማኖት ተቋማት መንፈሳዊ ስራ ላይ ጣልቃ መግባት እንደሌለበት ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም መንግስት የማህበረሰቡን ደህንነት እና ሰላማዊ መስተጋብር የማስከበር እንዲሁም የህግ የበላይነትን የማረጋገጥ ኃላፊነት እንዳለበት ከህገ-መንግስቱ አንቀጽ 13 እና ከህገ መንግስቱ ማብራሪያ አገላለጽ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም መብት በአፍሪካ ቻርተር የግለሰቦች እና ህዝቦች መብቶች አንቀጽ 8 ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የሰብዓዊ መብቶች ዓለም አቀፍ መግለጫ እና የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን አንቀጽ 18 ላይ ማንኛውም ሰው የሀሳብ፣ የህሊናና የሀይማኖት ነጻነት እንዳለው ይደነግጋሉ፡፡

## የኢሰመጉ ጥሪ፡

- ሀይማኖት የማህበራዊ መስተጋብር አንዱ ክፍልና መብት በመሆኑ መንግስት የማህበረሰቡን ሰላማዊ እንቅስቃሴ የማስጠበቅ ኃላፊነት እንዳለበት በመረዳት የፌደራል እና የክልል መንግስታት የዜጎችን ደህንነት እንዲያስከብር፣
- የፌደራል መንግስት እንዲሁም የክልል መንግስታት እና በዋናነት ችግሮች እየተፈጠሩበት ያለው የኦሮሚያ ክልል መንግስት የጸጥታ አካላት በቤተክርስቲያን እውቅና ያልተሰጣቸውን ኤጲስ ቆጶሳት በተለያዩ አብያተክርስቲያናት መመደብ አግባብ አይደለም በማለት የተቃወሙ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ላይ የሚፈጽሙትን ከህግ አግባብ ውጪ የሆነ ግድያ፣ አካል ማቁሰል፣ ድብደባ እና እስር እንዲያቆሙ እንዲሁም ከቅዱስ ሲኖዶስ በተላለፈው መልእክት መሰረት ጥቁር ልብስ የለበሱ ሰዎች ላይ የሚፈጸሙ እስሮች እና ድብደባዎችን እንዲያስቆም፣ ከህግ አግባብ ውጪ ግድያ፣ እስራት፣ ደብደባ እና ሌሎችም የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የፈጸሙ የጸጥታ አካላትን መንግስት በህግ ተጠያቂ እንዲያደርግና ይህንንም ለህዝብ ይፋ እንዲያደርግ እንዲሁም ጉዳዩ መፍትሄ እንዳያገኝና ወደ ግጭት እንዲቀየር ለማድረግ ነገሮችን ወደ ሌላ አቅጣጫ የሚስቡ አካላት ሁሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ኢሰመጉ በዚህ አጋጣሚ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ